የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት

በጉራጌ ዞን መስተዳድር

# የ1998/98 እና የ1999/2000 ምርት ዘመን የግብርናና ገጠር ልማት እቅድ

ሚያዝያ 1998

ወልቂጤ

# በጉራጌ ዞን መስተዳድር የ1998/98 እና የ1999/2000 ምርት ዘመን
# የግብርናና ገጠር ልማት እቅድ

## 1. መነሻ ሁኔታ

- የዞኑ አርሶ አደር በተለያዩ አግሮኢኮሎጂዎች የሚገኝ እንደመሆኑ በሰብል ልማትም ሆነ እንስሳት እርባታ በተለምዷዊ አሠራር ወይም በባህላዊ የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ሲያደርግ መቆየቱ፣
- በየዓመቱ የግብርናና የገጠር ልማት ዕቅዶችን በማዘጋጀት በተካሄደው እንቅስቃሴ የአርሶ አደሮችን ኑሮ ለመለወጥና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ መቻሉ፣
- ይሁንና በዞኑ ካለው አርሶ አደር ብዛት አንፃርና ካለው የድህነት ደረጃ አኳያ ሲታይ የተሰራው ሥራ በቂ እንዳልሆነና ባፋጣኝ ችግሩ ሊወገድ የሚችልበት መንገድ ካልተመቻቸ ዞኑ ወደ ባሰ ኢኮኖሚያዊ ችግር እንደሚገባ ያለው ሁኔታ በግልፅ ያስረዳል፡፡

ለዚሁም መገለጫ የሚሆኑት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው

- የግብርና ልማት ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ አርሶ አደሩ የምግብ ፍጆታውንና ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችለው አቅም ፈጥሮ መንቀሳቀስ ባለመቻሉ አስተማማኝ ገቢ እያገኘ አለመሆኑና በዚህም ምክንያት በአብዛኛው ከጉልበት ሥራ፣ ከብድር (ከአራጣ ብድር)፣ ከተለያዩ ቁሳቁስ ሽያጮች እንዲሁም በስፋት ከከተማ የሚደረግለትን ድጎማ የመጠበቁ ሁኔታ መታየቱ፡፡ ይህም ሁኔታ አርሶ አደሩን በራሱ አቅም ገቢውን ለማሳደግ የሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስን እንዲሆኑ ከማድረጉም ባሻገር ከጠባቂነትና ከተመፅዋችነት ያልተላቀቀ መሆኑን
- በእርሻ ሥራም ሆነ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት አላስፈላጊ የሆኑ ከፍተኛ ወጪዎችን የማውጣት ሁኔታ እንደ ባህል ማየትና ወጪው የማምረቻ ወጪ ነው በሚል የማሰብና ግብርና ትርፋማ አይደለም የሚል አስተሳሰብ መያዝ፣
- እንዲሁም ከንግድ ሥራ ውጪ በግብርናው ላይ እድገት አላገኝም በሚል አመለካከት መታጠር፣ እና ሌሎችም ምክንያቶች አርሶ አደሩ በግብርናው ሥራ ላይ ጠንክሮ እንዳይሰራ የአመለካከት ተጽዕኖዎች ከማሳደራቸውም ባሻገር የገቢው ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ አድርገዋል፡፡
- በሌላም በኩል አርሶ አደሩ የግብርና ሥራውን አጠናክሮ ለመሥራት ያለው ተነሳሽነት አነስተኛ በመሆኑ የተወሰኑ ሰብሎችን በማምረት ላይ ብቻ የማተኮር፣ አግባብነት ያለው የምርት ግብዓት አለመጠቀም (ማዳበሪያና ምርጥ ዘር፣ በሪኮመንዴሽኑ መሠረት ባለመጠቀሙ ምርትና ምርታማነት ዝቅተኛ መሆኑ)፣ የዞኑ አርሶ አደር ኋላቀር በሆነ የአመራረት ዘዴ ላይ ይገኛል፡፡

- የመሬት ጥበት ችግርን እንደ ዋነኛ ምክንያት በመውሰድና በጓሮ ያለውን ማሳውን በተቀናጀ የግብርና አሰራር ላይ ካለማዋል ጋራ በተገናኘ ምክንያት ምርታማነቱ ሊቀንስ ችሏል። ከዚሁ በተጨማሪ አመራረቱም ገበያ ተኮር ባለመሆኑ የየወቅቱን የገበያ ሁኔታ መሠረት ባደረገ መልኩ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በመለየትና በማምረት የሚያደርገው ጥረት ውስን ነው።
- አርሶ አደሩ ያለውን ሀብት ሙሉ በሙሉ አሟጦ በግብርናው የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ባለመጠቀሙና በበቂ ሁኔታ ባለማምረቱ እንዲሁም በስፋት ጥቅም ላይ ያልዋለውን የውሃ ሀብት ለመጠቀም የሚደረገው ጥረት አነስተኛ መሆን፣
- የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መሠረት ያደረገ የተቀናጀ የግብርና ልማት በአርሶ አደሩ ዘንድ አለመዳበር ያሉትን ችግሮች ይበልጥ እንዲሰፉ አድርጓቸዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ በቀጣይ የዞኑን አርሶ አደር ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ተጨባጭነት ወዳለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲገባ በማድረግ

- ያለውን ሀብት ማለትም መሬት፣ የውሃ ሀብት እንዲሁም የአርሶ አደሩ የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በአግባቡ ተጠቅሞ፣ የመላውን አርሶ አደር ንቅናቄ መሠረት ባደረገ መልኩ በየአካባቢው በሚካሄድ የግብርና ስራ ላይ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችል፣
- ከጠባቂነት፣ ከተመፅዋችነት እንዲሁም ከሌሎች የአመለካከት ችግሮች ተላቆ አሁን ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃና የገቢ አቅም ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያድግ ለማስቻል፣

ቀደም ሲል በዞኑም ሆነ በወረዳ ደረጃ የተዘጋጁትን የግብርናና የገጠር ልማት ዕቅዶች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመጠቀምና ይበልጥ በማዳበር ይህን ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. የሚከናወኑ ተግባራት

### *2.1.የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫዎች*

- የዞኑ ሕዝብ አብዛኛው አርሶ አደር እንደመሆኑ የልማቱም አቅጣጫ በዋነኛነት መሠረት የሚያደርገው በገጠር ልማት ላይ ነው። ስለዚህም በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ ሁሉም አስፈፃሚ/ፈጻሚ አካላት በቂ ግንዛቤና እምነት ጨብጠው መንቀሳቀስ ያለባቸው ሲሆን፣ በመሆኑ በዋነኛነት አርሶ አደሩና በየደረጃው ያሉ የግብርናና የገጠር ልማት ባለሙያዎች አስተያየት ሰጥተውበትና አምነውበት እንዲገቡ ማስቻል።
- በየደረጃው ያሉ የግብርናና ገጠር ልማት ባለሙያዎች ኃላፊነትን ከተጠያቂነት መስጠት፣

- በሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ የወጣቶችና የሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ መጠናከር ይኖርበታል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ዕቅድ በማዘጋጀት በየወረዳው ያሉ ወጣቶች/ሴቶች ወደ ልማት ሊገቡ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የግብርናና የገጠር ልማት ሥራዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በት/ቤቶች አካባቢ የሚሠራው ሥራ ወሳኝነት አለው፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ ት/ቤት ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ በግብርናና ገጠር ልማት ሥራዎች ላይ ቀደም ሲል ሲሰጥ ከነበረው ሁኔታ ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ለተማሪዎች በተቻለ መጠን ተግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ስለ ግብርና ልማት ትምህርት መስጠት፣
- አርሶ አደሩ ከኢኮኖሚ አንፃር ራሱን ችሎ እንዳይንቀሳቀስ ከሚያደርጉት መሠረታዊ ችግሮች መካከል ዋናዎቹ የሥራ ባህል አለመዳበር፣የቁጠባ ባህል አለመኖር፣ኋላቀር የሆኑ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ተጽእኖዎቹ በልማቱ ሥራ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛል፡፡ ስለዚህም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የአመለካከት ለውጥን በአርሶ አደሩ ዘንድ ማምጣት የሚጠይቅ በመሆኑ በደጋፊ አደረጃጀቶችና የሃይማኖት ተቋማት ላይ ሰፊ ሥራ የመስራትና ተልዕኮ የመስጠት ሥራ መከናወን አለበት፡፡
- በዞኑ በአሁኑ ወቅት እየተንቀሳቀሱ ያሉ በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/NGO'S/ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዞኑ ውስጥ ካሉትም ሆነ በቀጣይ ለመግባት ፍላጐቱ ካላቸው NGOS ጋር ዞኑ በያዘው የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ አንፃር ድጋፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት ሁኔታና በቀጣይም በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በግብርናው ሥራ ላይ አምራች የሆነውን ሃይል እየጐዱ ካሉት በሽታዎች መካከል HIV/AIDS እንዲሁም የወባ በሽታ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስለዚህም ቀደም ሲል በዞንም/በወረዳ ደረጃ ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ከላይ የተጠቀሱትን በሽታዎች ለመከላከል ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ይህንኑ ይበልጥ ለማጠናከር እንዲቻል የሚመለከታቸው አካላት እስከ አሁን ያለውን አፈፃፀም በመገምገም የሚታዩ ዋነኛ ችግሮችን በመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ በተጠናከረ መልኩ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡

ስለዚህም ከላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

## *2.2. በአርሶ አደሩ ዘንድ ንቅናቄ በመፍጠር የሚሠሩ ሥራዎች፣*

### *2.2.1 የአርሶ አደሩን አመለካከት ከመለወጥ አንፃር መከናወን ያለባቸው ሥራዎች*

**የሥራ ባህል ማሻሻል በተመለከተ**፡- አርሶ አደሩ ጉልበቱን በአግባቡ ያለመጠቀም ችግር በስፋት ጉልቶ ይታይበታል፡፡ ስለዚህም የሥራ ባህሉን ከማሻሻል አንፃር ከላይ በዕቅድ አፈጻጸም አቅጣጫ ላይ በተቀመጠው መሠረት በዕቅድ የሚመራና ተከታታይነት ባለው መልኩ አመለካከትን የመለወጥ ሥራ

*መሥራትና ለውጥ እያመጡ ያሉ አርሶ አደሮችን የመለየትና የማበረታቻ ሥራዎች መከናወን* አለባቸው::

**የቁጠባ ባህል ለማሳደግ፡-** ለዞኑ አርሶ አደሮች ድህነትንና ራስን አለመቻል ዋነኛው ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ የገቢ አያያዝና የተገኘውን ገቢ በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል አለመቻል መሆኑ ይታወቃል:: በአብዛኛው የዞኑ አርሶ አደሮች የእርሻ እቅድ አዘጋጅተው ወጪና ገቢያቸውን አስልተው ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነውን የመቆጠብ እውቀታቸውና ልምዳቸው ዝቅተኛ ነው:: ስለዚህም የቁጠባ ኤክስቴንሽን በስፋት አርሶ አደሩ ዘንድ ማድረስና በዕቅድ ላይ በተመሠረተ መልኩ የቁጠባ ማሕበራት የማደራጀት *ሥራ* በስፋት *መሠራት ያለበት* ሲሆን፣ በዚህም የሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ መጠናከር አለበት::

## *2.3. አግሮ ኢኮሎጂን መሠረት ያደረገ የግብርና ልማት እንቅስቁሴን ማካሄድ፣*

የአርሶ አደሩን የገቢ አቅም ከማሳደግ አንፃር አግሮ ኢኮሎጂን *መሠረት ያደረጉ* ከዚህ በታች የተገለፁ *ሥራዎች መከናወን* አለባቸው::

የጉራጌ ዞን በሁለት የአግሮ ኢኮሎጂ ቀጠናዎች የሚከፈል ሲሆን እነዚህም በቂ ዝናብ የሚያገኙና የዝናብ እጥረት ያለባቸው በሚል የተከፈሉ ናቸው:: በዚሁ *መሠረት*

- <u>በቂ እርጥበት</u> የሚያገኙት ወረዳዎች ቸሃ፣ እነሞርና ኤነር፣ እዣ፣ ምሁርና አክሊል፣ ኮኪር፣ ጉመር፣ ቀቤና፣ ከፊል አበሽጌና እንደጋኝ ወረዳዎች ሲሆን
- የእርጥበት ችግር ያለባቸው መስቃን፣ ማረቆ፣ ሶዶ፣ ከፊል እነሞር ከፊል አበሽጌ እንዲሁም የቸሃ ቆላማውን ክፍል የሚያጠቃልል ነው::
- ስለዚህም የሚካሄዱት የግብርና ልማት *ሥራዎች* አግሮ ኢኮሎጂን *መሠረት* ባደረገ መልኩ መከናወን ያለባቸው ሲሆን በዋነኝነትም በቂ እርጥበት በሚያገኙ አካባቢዎች <u>ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ</u> ትኩረት የሚሰጥበት ተግባር ነው:: በዚሁ *መሠረት* በ1998/99 ምርት ዘመን ከዞኑ ከፍተኛ ምርት የሚጠበቅ ሲሆን ዝርዝሩ በየወረዳው በሚታረስ የመሬት መጠንና በሚጠበቅ የምርት መጠን በየወረዳዎች ተቀምጧል::

የዝናብ እጥረት ባለባቸውም አካባቢዎች <u>የውሃ *ሥራዎችን መሠረት ያደረገ*</u> የልማት እንቅስቃሴ ማካሄድ የግድ ነው:: ከላይ የተጠቀሱትን ሃሣቦች *መሠረት* በማድረግ በየአግሮ ኢኮሎጂዎቹ የሚሠሩ *ሥራዎች* ከዚህ እንደሚከተሉት ናቸው::

### 2.3.1. በቂ እርጥበት በሚያገኙ አካባቢዎች የሚከናወኑ *ሥራዎች*፣

#### 2.3.1.1 ሰብል ልማትን በተመለከተ

- <u>*ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣*</u>

- ምርታማነት በእነዚህ አካባቢዎች ማሳደግ ቁልፍ ተግባር ሲሆን ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ የማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር አጠቃቀም በፓኬጅ ላይ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ተግባራዊ ለማደረግ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችም ሆነ የግብርና ባለሙያዎች በሚጠበቀው መልኩ ከመቼውም ጊዜ በተጠናከረ መልኩ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- በተለይም የግብአት ዋጋ ተወዷል የሚለው የአርሶ አደሩን አስተሳሰብ ለማስወገድ በተግባር ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ይህን የአመለካከት ችግር ሊወገዱ የሚችልበት ሁኔታ መቀየስና አርሶ አደሩ የተለያዩ ግብአቶችን በአግባቡ ከተጠቀመ ብዙ ምርት ማግኘት እንደሚችል ትርፋማ ከመሆን የሚያግደው ነገር እንደሌለ አርሶ አደሩን ማሳመን ይገባል፡፡
- በዚሁ መሠረት የምርታማነት ደረጃ በዋና ዋና ሰብሎችና በአምራች ወረዳዎች በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን መድረስ ያለበትን የምርታማነት መጠን በተመለከተ ለየሰብሉ በተዘጋጀው የፓኬጅ ዶክመንት ላይ በተቀመጠው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

| ተራ ቁጥር | ወረዳ | የሰብል ዓይነት | አሁን ያለው ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) | በ1998/99 መደረስ ያለበት ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጉመር | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 16 | 50 |
| | | ገብስ | 18 | 30 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 11 | 25 |
| | | ባቄላ | 14 | 20 |
| | | የሥራ ሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 90 | 150 |
| 2 | ምሁር አክሊል | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 22 | 50 |
| | | ገብስ | 18 | 35 |
| | | ጤፍ | 8 | 20 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 9 | 25 |
| | | ባቄላ | 9 | 20 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 70 | 123 |
| 3 | እዣ | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 24 | 50 |
| | | ገብስ | 18 | 30 |

| ተራ ቁጥር | ወረዳ | የሰብል ዓይነት | አሁን ያለው ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) | በ1998/99 መደረስ ያለበት ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|
| | | ጤፍ | 8 | 25 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 8 | 21 |
| | | ባቄላ | 11 | 20 |
| | | የቅባት ሰብል | | |
| | | ኑግ | 5 | 7 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 70 | 175 |
| 4 | እንደጋኝ | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 20 | 50 |
| | | ገብስ | 18 | 30 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 8 | 25 |
| | | ባቄላ | 8 | 20 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 95 | 175 |
| 5 | ኮኪር ገደባኖ | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 25 | 50 |
| | | ገብስ | 24 | 35 |
| | | ጤፍ | 10 | 25 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 10 | 21 |
| | | ባቄላ | 11 | 20 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 90 | 156 |
| 6 | ቀቤና | የአገዳ ሰብሎች | | |
| | | በቆሎ | 18 | 44 |
| | | ማሽላ | 12 | 18 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ጤፍ | 10 | 20 |
| | | ስንዴ | 23 | 50 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | ቦሎቄ | 9 | 16 |
| | | ሽምብራ | 8 | 16 |

| ተራ ቁጥር | ወረዳ | የሰብል ዓይነት | አሁን ያለው ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) | በ1998/99 መደረስ ያለበት ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|
| | | የቅባት ሰብል | | |
| | | ኑግ | 4 | 7 |
| 7 | እነሞርና ኤነር | የአገዳ ሰብል | | |
| | | በቆሎ | 22 | 43 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 15 | 50 |
| | | ገብስ | 12 | 30 |
| | | ጤፍ | 9 | 20 |
| | | የጥራጥሬ ሰብል | | |
| | | ቦሎቄ | 8 | 16 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 95 | 150 |

➢ <u>በአርሶ አደሩ ማሣ ላይ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ መረባረብ፣</u>

የግብርና ልማት ሥራዎች ተጀምረው እስከሚያበቁ ባሉት ጊዜያት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በጥራት ማከናወን የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡ በመሆኑም የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን በማሣደጉ በኩል በበጋው ወራት ከሚሠሩት ሥራዎች በመጀመር በቀጣይ በልግና መኸር የሚሠሩ ሥራዎች በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን ከወዲሁ ዕቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በሚኒመም ፓኬጅ ሆነ በቤተሰብ ፓኬጅ አማካይነት ምርትና ምርታማነትን በማሣደጉ በኩል ቀጣይ ተግባራት በአርሶ አደሩ ማሣ ላይ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

ከዚሁ አንጻር ትኩረት የሚደረግባቸው ተግባራት

- የማሣ ዝግጅት በጥራትና በፍጥነት ማከናወን፣
- በወቅቱና በተገቢው መንገድ የመዝራትን አስፈላጊነት ማስተማር ፣
- የማደበሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፣
- በወቅቱና በአግባቡ አረም የማረምና ለምርት እድገት መረባረብ እንዳለበት ማስተማር፣
- ልዩ ልዩ የርጥበት መጠበቂያ ዘዴዎችን አርሶ አደሩ በጥቅም ላይ እንዲያውል ማድረግ፣
- አዝመራ በወቅቱ የመሰብሰብ አስፈላጊነትን ማስተማር፣
- የመስኖ አውታሮችንና ሌሎች የውሃ አጠቃቀም ዘዴዎች በሙሉ አቅም በግብርና ልማት ላይ ማዋል፣

- **የኮትቻ አፈር ውሃን ማጠንፈፍን በተመለከተ** በዞኑ የኮትቻ አፈር በቀላሉ በአበሸጌ፣ ቀቤና፣ ሶዶ፣ ኮኪር ወረዳዎች ሰፊ ቦታዎች የሚገኙ ሲሆን ውሃ ማጠንፈፍና የተጠራቀመውን ውሃ በጥቅም ላይ በማዋል ከዋናው የመኸር ሰብል ጋር ተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡

- **በፍራፍሬ ልማት በስፋት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣** ይኸውም ዞኑ ከአለው አግሮኢኮሎጂ አንፃር ከደጋ ፍራፍሬ ፓም፣ፒር፣ኘላምና ኮክ ከወይና ደጋና ቆላ የፍራፍሬ ሰብሎች አቮካዶና ማንጐ ለማምረት አመቺ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህን የፍራፍሬ ሰብሎች በአርሶ አደሩ፣በመንግሥት ችግኝ ጣቢያዎች የተሻሻሉ የደጋ ፍራፍሬና የወይናደጋ/ፍራፍሬ ሰብሎች ችግኞችን በማምረት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- **ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣** ምርት ከተመረተ በኋላ የምርት ብክነት እንደሚከሰትና እስከ አሁን ካለው መረጃ ከ35-40% የምርት ብክነት እንደሚኖር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንኑ ችግር ለመቀነስ አርሶ አደሩ የተሻሻሉ የጐተራ አሠራሮችን ሠርቶ በጥቅም ላይ እንዲያውል በሠርቶ ማሣያዎች የተጠናከረ ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ሲሆን ለዚሁ አፈጻጸም በተዘጋጀው ፓኬጅ ላይ ለባለሙያዎችም ሆነ ለአርሶ አደሮች ተግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡
- **የሐር ልማት፣** አብዛኛውም አርሶ አደር የእርሻ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ ቀሪውን የበጋ ጊዜ ያለሥራ እንደሚያሳልፍ ነው፡፡ ስለሆነም የሐር ልማት በመጀመሪያ ከአነስተኛ መሬት በአንፃራዊ መልኩ ከሰብል ልማቱ የተሻለ ገቢ የሚያስገኝ፣ በሁለተኛ ደረጃ የሐር ልማትን ዓመቱን በሙለ ማካሄድ የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሩና ቤተሰቡ ዓመቱን ሙሉ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

2.3.1.2 **እንስሳት ሀብት ልማትን በተመለከተ፣**

የእንስሳት ሀብት ልማት በመደበኛና በቤተሰብ ፓኬጅ የሚከናወን ሲሆን ይህም በዋናነት በሚከተሉት ተግባራት ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

- **የእንቁላልና የዶሮን ምርት ማሻሻል፣** የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ከማሰራጨት አንፃር የሶስት ወር አውራ ዶሮና ቄብ ከማሰራጨት በተጨማሪ የአንድ ቀን ዕድሜ ያላቸውን ጫጩቶችና ለም እንቁላሎችን በማሰራጨት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ ሥራ መከናወን ይኖርበታል፡፡ በተለይም የአንድ ቀን ጫጩቶችን የመጠቀም ሁኔታ /HAY-BROODER/ ከፍተኛ ዶሮ አምራች በሆኑና ተስማሚነት ባላቸው አካባቢዎች ይከናወናል፡፡
- **የወተትና የወተት ምርት ተዋጽዎችን ማሻሻል፣** የወተት ምርት አሁን ካለበት ደረጃ ለማሻሻል የሰው ሠራሽ የእንስሳት ማዳቀያ አገልግሎት በስፋት መካሄድ አለበት፡፡የሰው ሠራሽ የእንስሳት የማዳቀል

አገልግሎትን ከማጠናከርና ከማስፋፋት አንፃር በተለያዩ የገጠር ቀበሌዎችና በከተማ አካባቢ በተገነቡ የማዳቀያ ጣቢያዎች በመጠቀም አዳቃይ ቴክኒሺያኑ አገልግሎት መስጠት አለበት።

የእንስሳት ሀብት ልማቱን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የመኖ ልማት ጐን ለጐን ማካሄዱ አስፈላጊ ነው።

- **የሥጋ ምርት ማሻሻል፣** ለእንስሳቶች የተሟላ የመኖና የውሃ አቅርቦት በተከታታይ እንዲያገኙ በማድረግ የተለያዩ የቀንድ ከብቶችን እያደለቡ በተሻለ ዋጋ በገበያ ላይ እንዲሸጡ በማድረግ አርሶ አደሩ ጥሩ ዋጋ የሚያገኝበት ሥራዎች ይከናወናሉ።

2.3.1.3 **የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ፣**

- በቂ የእርጥበት መጠን ባለባቸው አካባቢዎች የተፈጥሮ ደኖች የሚገኝ እንደመሆኑ በእነዚያ አካባቢዎች የምናካሂዳቸው ሥራዎች ያለውን የተፈጥሮ ሀብት መሠረት ባደረገ መልኩ የሚከናወን ነው።
- በዚሁ መሠረት የተፈጥሮ ደኖችን የመጠበቅና በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የተፈጥሮ ደን በተራቆተባቸውና የአፈር መሸርሸር ባለባቸው አካባቢዎች ተፋሰስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ የአፈር ጥበቃና ልማት እንዲሁም የደን ልማት ሥራዎች ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ ይከናወናሉ።

2.3.2 **በእርጥበት አጠር ወረዳዎች የሚከናወኑ ተግባራት፣**

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በዞኑ በእርጥበት አጠር የሚመደቡት ወረዳዎች መስቃን፣ ማረቆ፣ ሶዶና ክፌል እ/ሞርና ኤነር በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎችም ከፍተኛ የዝናብ እጥረትና መቆራረጥ የሚያጋጥማቸውና የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ችግር በስፋት የሚታይባቸው ናቸው።

ስለዚህም በእነዚህ ወረዳዎች የሚከናወኑ ስራዎች የሚከተሉትን የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወኑ ይሆናሉ፡-

- ውሃ ማሰባሰብን ማዕከል ያደረገ የግብርና ልማት ሥራን ማከናወን፣
- እንስሳት ጤና አገልግሎትን ከማጠናከር አንፃር የክትባት አቅርቦት የቆላ ዝንብ ቁጥጥር፣ የበሽታ ክስተትና ፍንዳታ ቁጥጥር እንዲሁም የእንስሳት ጤና ክሊኒክ ግንባታ ሥራዎችን ማካሄድ
- የሥጋ ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አንፃር የበግና ፍየል እርባታን በስፋት ማካሄድና የሌጦ ምርት የማሻሻል ሥራዎች ማካሄድ፣
- የወተት ምርትን ከማሻሻል አንፃር የሰው ሰራሽ የእንስሳት ማዳቀል አገልግሎትን ማስፋፋት
- በአርሶ አደሩ ማሳ በሚሰሩ ስራዎች ላይ (በቂ እርጥበት ባላቸው አካባቢዎች በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ማከናወን) ትኩረት ማድረግ፤
- በጥራጥሬ፣ በብርዕ፣ በአትክልት፣ በሥራሥርና በቅመማቅመም ሰብሎች ላይ ትኩረት ማድረግ፣

- ምርታማነታቸውን በተመለከተ በፓኬጁ ላይ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፣
- ተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ተፋሰስን መሰረት ባደረገ መልኩ የደን ልማትና የአፈር ጥበቃ ስራዎችን ማከናወን፣
- በቤተሰብ ደረጃ የሚካሄደውን የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰፈራ ፕሮግራም ማካሄድ፣ ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ተግባራዊ በማድረግ ከምርታማነት አንጻር አሁን ያለበትን ደረጃና በቀጣይ መደረስ ያለበት የምርታማነት መጠን በየወረዳው ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | ወረዳ | የሰብል ዓይነት | አሁን ያለው ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) | በ1998/99 መደረስ ያለበት ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መስቃን | የአገዳ ሰብሎች | | |
| | | በቆሎ | 16 | 43 |
| | | ማሽላ | 12 | 24 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 25 | 50 |
| | | ገብስ | 14 | 30 |
| | | ጤፍ | 9 | 25 |
| | | የጥራጥሬ ሰብል | | |
| | | ቦሎቄ | 12 | 16 |
| | | የቅመማቅመም ሰብል | | |
| | | በርበሬ | 6 | 12 |
| 2 | ማረቆ | የአገዳ ሰብሎች | | |
| | | በቆሎ | 18 | 43 |
| | | ማሽላ | 14 | 18 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 23 | 50 |
| | | ጤፍ | 6 | 25 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | ቦሎቄ | 7 | 16 |
| | | የቅመማቅመም ሰብል | | |
| | | በርበሬ | 7 | 12 |
| 3 | ሶዶ | የአገዳ ሰብሎች | | |
| | | በቆሎ | 23 | 43 |
| | | ማሽላ | 13 | 18 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 18 | 50 |
| | | ገብስ | 14 | 30 |
| | | ጤፍ | 10 | 20 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | አተር | 7 | 21 |
| | | ባቄላ | 9 | 20 |
| 4 | አበሽጌ | የአገዳ ሰብሎች | | |
| | | በቆሎ | 26 | 43 |
| | | ማሽላ | 14 | 18 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |

| ተራ ቁጥር | ወረዳ | የሰብል ዓይነት | አሁን ያለው ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) | በ1998/99 መደረስ ያለበት ምርታማነት (ኩ/ል በሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|
| | | ጤፍ | 10 | 20 |
| | | የጥራጥሬ ሰብሎች | | |
| | | ሽምብራ | 9 | 16 |
| | | ቦሎቄ | 11 | 16 |
| | | የቅባት ሰብሎች | | |
| | | ኑግ | 5 | 7 |
| | | ሰሊጥ | 3 | 7 |
| | | የቅመማቅመም ሰብል | | |
| | | በርበሬ | 8 | 12 |
| 5 | ቸሃ | የአገዳ ሰብል | | |
| | | በቆሎ | 22 | 43 |
| | | የብርዕ ሰብሎች | | |
| | | ስንዴ | 20 | 50 |
| | | ገብስ | 18 | 30 |
| | | ጤፍ | 11 | 25 |
| | | የሥራሥር ሰብል | | |
| | | ድንች | 95 | 150 |

## *2..4 በሁሉም የዞኑ አካባቢዎች መተግበር ያለባቸው ሥራዎች*

- **ኅብረት ስራ ማህበራትና ግብይት በተመለከተ፣**
  - አዳዲስ ማህበራትን ማደራጀት
  - ነባር ማህበራትን ማጠናከር
  - የግብይት ስራ ማጠናከር
- **የግብዓት አቅርቦቶችን ማካሄድ (ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር)**
- **የምግብ ዋስትናን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የሴፍቲኔት ኘሮግራም በተመለከተ**
  - በተደጋጋሚ ድርቅ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ላይ ትኩረት የማድረግ
  - ተጠቃሚዎችን በአግባቡ የመለየትና በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራዎች ይከናወናሉ

## 3. <u>በ1998/99 እና በ1999/2000 የሚከናወኑ ስራዎች ዝርዝር ዕቅድ</u>

*የዞኑን የግብርና ልማት ዝርዝር አፈፃፀምን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑትን ሥራዎች ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባትና በመገምገም በቀጣይ መሠራት ለሚገባቸው ሥራዎች የአፈጻጸም ስልትና መመሪያ በማዘጋጀት ሥራዎችን አጐልብቶ የማከናወን ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚሁ መሠረት :-*

### 3.1 *<u>የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በሚመለከት</u>*

- የልማት ሠራተኞችን አቅም ከማሳደግ አንፃር በተለያዩ ምክንያቶች ኮሌጅ ገብተው ለመማር እድል ያላገኙት 121 የልማት ሠራተኞች ኮሌጅ ገብተው በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ ይደረጋል።
- የአርሶ አደሩን የግብርና ክህሎት ከማሳደግ አንፃር፣ በሞጁላር ሥልጠና ስፔሻላይዜሽንን መሠረት ባደረገ መልኩ በ1999 ዓ.ም 11¸160 አርሶ አደሮች ቀደም ሲል በተገነቡት ገማግ ይሠለጥናሉ።
- በሚኒመም ፓኬጅ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በአጠቃላይ በዞኑ የሚገኙ አባወራ አርሶ አደሮች በሙሉ ተጠቃሚ ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ እስከ 1999 መጨረሻ 120¸636 አርሶአደሮች የሚሠለጥኑ ይሆናል።
- በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ኅ/ሥ/ማኅበራት አደረጃጀትና አሠራር ዘመናዊ ለማድረግ
    - ለ38 ለኅብረት ሥራ ዘርፍ ባለሙያዎች፣
    - ለ932 የኅብረት ሥራ አመራሮች፣
    - ለ41 የኅ/ሥ/ማኅበር ቅጥር ሠራተኞችና
    - ለ35¸386 የኅ/ሥ/ማ አባልና አባል ላልሆኑ አርሶ አደሮች በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል።
- የህብረተሰባችን ግማሽ አካል የሆኑትን የሴት አርሶ አደሮች ኑሮአቸውን ለማሻሻልና ገቢያቸውን ለማሣደግ በሚደረገው ጥረት ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ የገቢ ምንጫቸውን ለማሣደግ በተለያዩ ፓኬጆች እንዲሳተፉ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል።

## 3.2 <u>ምርትና ምርታማነትን ከማሣደግ አንፃር</u>

በያዝነው ምርት ዘመንና በ1999/2000 ምርት ዘመን የሰብል ምርትና ምርታማነትን ከማሣደግ አኳያ ቀደም ሲል ሥነ-ምህዳርን መነሻ በማድረግ የተነደፉት የስፔሻላይዜሽን ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። በዚሁ መሠረት:-

### 3.2.1 <u>ከስፔሻላይዜሽን አኳያ</u>

ዞኑ የተለያየ ስነ-ምህዳር ያለው እንደመሆኑ በገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶችን በስፔሻላይዜሽን ኘሮግራም በዋናነት ሊመረቱ የሚችሉ ሽንብራ፣ ጤፍ፣ ቡና፣ ፍራፍሬ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ በርበሬ በእንስሳት ሀብት ልማት ማድለብ፣ ማርባት ... ወዘተ ከዚህ በፊት የነበረው የአመራረት ልምድ እና ለግብርና ምርቶች ተስማሚ የስነ-ምህዳር ቀጠናዎችን ታሳቢ ማድረግ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት የስፔሻላይዜሽን ኘሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል።

| ተ/ቁ | የወረዳው ስም | በወረዳው እስፔሻላይዜሽን ሲያደርጉ የግብርና ምርቶች |
|---|---|---|
| 1 | አበሽጌ | ሽምብራ፣ጤፍ፣ የወተት ሀብት ልማት፣ ማድለብ፣ ሰሊጥ፣ቦለቄ፣እኩሪ አተር፣ኑግ |
| 2 | ቀቤና | ሽምብራ፣ጤፍ ኑግ፣ ማድለብ |
| 3 | ቸሃ | ቡና፣ጤፍ፣ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሰሊጥ |
| 4 | እ/ኤነር | ቡና፣ጤፍ፣ ማንጎ፣አቮካዶ፣ ሰሊጥ |
| 5 | ጉመር | አተር፣ነጭ ሽንኩርት፣ የደጋ ፍራፍሬ፣ የወተት ሀብት ልማት፣ ማድለብ |
| 6 | እንደጋኝ | ስንዴ፣አተር፣ማድለብ፣ነጭሽንኩርት |
| 7 | እዣ | አተር፣ስንዴ፣ ፍራፍሬ፣ ማድለብ፣ነጭ ሽንኩርት፣የደጋ ፍራፍሬ፣ አትክልት |
| 8 | ም/አክሊል | አተር፣ ነጭ ሽንኩርት፣ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ማድለብ፣ የደጋ ፍራፍሬ |
| 9 | ኮኪር | ስንዴ፣አተር፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ማድለብ |
| 10 | ሶዶ | ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማድለብ፣ አትክልት ማንጎ አቮካዶ |
| 11 | መስቃን | በርበሬ፣ጤፍ፣ ማድለብ፣ወተት ሀብት ልማት ማንጎ፣ አቮካዶ፣አትክልት፣ቦሎቄ፣አኩሪአተር |
| 12 | ማረቆ | በርበሬ፣ ስንዴ፣ ቦሎቄ፣ ፍየል እርባታ |

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በአጠቃላይ በዞኑ ከስፔሻላይዜሽን አንጻር በቀጣዩ ሁለት ዓመታት የሚለማ መሬትና ሊመረት የታቀደ ምርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በ1997/98 የምርት ዘመን በጥራጥሬ፣ በቅባት፣ በቅመማ ቅመም ሰብሎች በድምሩ 36325 ሄ/ር ለምቶ የነበረውን መሬት በ1998/99 ወደ 39¸832 ሄ/ር እንዲሁም በ1999/2000 ወደ 44912 ሄ/ር በማሣደግ ከዚህም ቀደም ሲል ከእነዚህ ሰብሎች ይገኝ የነበረውን 304¸277 ኩ/ል በ1998/99 ወደ 641¸649 ኩ/ል በ1999/2000 1¸095¸121 ኩ/ል ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተለይም ከጥራጥሬ ሰብሎች በቦሎቄና ሽምብራ፣ ከቅባት ሰብሎች በሰሊጥ፣ ከቅመማ ቅመም በበርበሬ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
- በፍራፍሬ ልማት ዘርፍ አርሶ አደሩ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን ዞኑ ካለው ተስማሚ ሥነ ምህዳር አንፃር የደጋና የቆላ ፍራፍሬዎች ልማትን በማስፋፋት እስከአሁን በዞኑ ለምቶ የሚገኘውን 4¸736 ሄ/ር እስከ 1999/2000 8¸118 ሄ/ር ለማሳደግ እቅድ ተይዟል፡፡
- ምንም እንኳን ዞኑ በከፍተኛ ቡና አብቃይ ደረጃ ባይመደብም በተወሰኑ ወረዳዎች በመመረት ላይ የሚገኘው ምርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከምርምር ማዕከላትና በአካባቢው በምርታማነታቸውና የቡና ፍሬ በሽታን በመቋቋም የሚታወቁ ዝርያዎችን በመለየት እስከ 1997 ዓ.ም በዞኑ የለማውን 8202 ሄ/ር ቡና በ1999/2000 ወደ 10485 ሄ/ር የሚደርስ ሲሆን የቡና አቅርቦትም በሚመለከት በ1997/98 ዓ.ም 27000 ኩ/ል የነበረው እስከ 1999/2000 40570 ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል፡፡

3.2.2 ሌሎች በዞኑ የሚመረቱ ዋና ዋና ሰብሎች ምርትና ምርታማነትን ከማሣደግ አኳያ

- የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን እንደዚሁም ገቢውን ለማሣደግ የእርጥበት ችግር በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው ወረዳዎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተጠናከረ መልኩ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን መስጠት፡፡
- በተለይም የእርጥበት ችግር በሌለባቸው አካባቢዎች በዓመት 2 ጊዜና ከዚያ በላይ በማምረት እንደዚሁም የኮትቻ አፈር በሚገኝባቸው ወረዳዎች በተለይም በአበሽጌና በቀቤና ወረዳዎች አርሶ አደሩ ውሃን በማጠንፈፍ በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት የሚችልበትን የአመራረት ዘዴ በማስተማር
- የውሃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂዎችንና ዘመናዊና ባሕላዊ የመስኖ አውታሮችን በሙሉ አቅማቸው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡

በዚሁ መሠረት

- በብርዕ፣ በአገዳ፣ በጥራጥሬና በቅባት ሰብሎች በ1997/98 146¸259 ሄ/ር ለምቶ 2¸244¸578 ኩ/ል ይገኝ የነበረውን በ1998/99 164¸058 ሄ/ር በማልማት 5¸148¸081 ኩ/ል ምርት በ1999/2000 193¸239 ሄ/ር በማልማት 6¸102¸011 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዷል፡፡
- የእርጥበት ችግር በአለባቸው የዞኑ አካባቢዎች የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጡ አንፃር በቤተሰብ ደረጃ የተገነቡ የውሃ ማሰባሰቢያ ገንዳዎችንና ሌሎች የውሃ አጠቃቀም ቴክኖሎጂዎችንና ዘመናዊና ባሕላዊ የመስኖ አውታሮችን በሙሉ አቅም በመጠቀም በ1997/98 ዓ.ም 1855 ሄ/ር ለምቶ 177¸115 ኩ/ል ምርት ይገኝ የነበረውን በ1998/99 ዓ.ም ወደ 2525ሄ/ር በ1999/2000 3235 ሄ/ር የሚደርስ ሲሆን ከዚህም በ1997/98 351¸536 ኩ/ል በ1999/2000 390¸236 ኩ/ል ምርት ይገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡
- በአጠቃላይ በአገዳ፣ በብርዕ፣ በጥራጥሬ፣ በቅባት፣ በቅመማ ቅመም፣ በሥራሥር፣ አትክልትና ፍራፍሬ በ**1997/98** ተመርቶ የነበረው **7.5** ሚሊዮን ኩ/ል ከላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በ1998/99 ዓ.ም 12¸949¸338 ኩ/ል በ1999/2000 ከ15 ሚሊዮን ኩ/ል በላይ ለማምረት ግብ ተጥሏል፡፡
- ምርትና ምርታማነትን ለማሣደግ ከሚያስፈልጉት ቴክኖሎጂዎች ዋነኛው የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የግብአት አቅርቦት ለልማት ግቦቻችን ውጤታማነት ወሳኝ በመሆኑ ሥነ ምህዳርን ባገናዘበ መልኩ የተጠናከረ የግብአት አቅርቦትና ሥርጭት በማድረግ አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ስለሆነም የማዳበሪያና የምርጥ ዘር አጠቃቀማችን በፓኬጁ በተቀመጠው ጥንቅር መሰረት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

## 3.4 <u>በእንስሳት ሀብት ልማት</u>

በንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚው ባለፈው የመርሐ ግብሩ-ዓመታት ለዞኑ አርሶአደር በቀረቡት የተለያዩ የእንስሳት ሀብት ልማትን ምርት ማሣደግ በሚችሉ የተለያዩ ፓኬጆች ተጠቃሚ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በመጪው የእቅድ ዓመታት በመደበኛና በቤተሰብ ፓኬጅ በዋናነት በሚከተሉት ተግባራት ላይ ያተኮረ ሥራ ይከናወናል፡፡

- የሰው ሠራሽ እንስሳት የማዳቀል አገልግሎትን በማጠናከርና በማስፋፋት በ1997/98 2066 የነበረውን የእንስሳት ማዳቀል አገልግሎት በ1998/99 4323 እንዲሁም በ1999/2000 ዓ.ም ወደ 6484 በማሳደግ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለማራባት ታቅዷል፡፡
- የሥጋ ምርት ከማሻሻል አንፃር በዋነኛነት የቀንድ ከብቶችን የበግና ፍየል የአመጋገብ ሥርዓታቸውን በማሻሻል አርሶ አደሩ አደልቦ የተሻለ ገቢ ማግኘት እንዲችል የሚደረግ ሲሆን ይኸው በ1997/98 ዓ.ም 3983 የነበረውን የማድለብና የማሞከት ሥራ በ1998/99 ዓ.ም ወደ 9800 በ1999/2000 ወደ 14700 የተለያዩ  የቀንድ ከብቶችን የማድለብና የማሞከት ሥራ ይካሄዳል፡፡
- እያደገ የመጣው የተሻሻሉ ዶሮዎች  ፍላጐትን ለመቅረፍ በክልሉ የሚገኙትን የብዜት ሥራዎችን በስፋት በመጠቀም አውራና ቄብ የአንድ ቀን እድሜ ጫጩቶችን የማሠራጨት ተግባር በስፋት የሚካሄድ ሲሆን ይህንኑ ለመተግበር በ1997/98 11146 የነበረውን የዶሮ ሥርጭት በ1999/2000 ወደ 24000 የሚያድግ ይሆናል፡፡ ይሁንና እቅዱን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ሀገሮች በመከሰት ላይ የሚገኙ የአእዋፍ እንፍሉዌንዛ በሽታን ከግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡
- በዞኑ በተለያዩ ወረዳዎች በመመረት ላይ የሚገኘውን የማር ምርት ለማሻሻል የተሻሻሉ የንብ ቀፎዎችንና የማንቢያ ቁሳቁሶችን የመጠቀምና የአንቢው አርሶአደር አቅም የማሣደግ ሥራዎች የሚሠሩ ይሆናል፡፡ ከዚህም ጐን ለጐን በ1997/98 ዓ.ም 1052 የተሻሻሉ የንብ ቀፎዎች የተሠራጨ ሲሆን ይህንንም በቀጣዩ ዓመታት አርሶ አደሩን ግንዛቤ በማስጨበጥ እስከ 1999/2000 ዓ.ም 4110 የተሻሻሉ የንብ ቀፎዎችን በመጠቀም በ1997/98 ዓ.ም 54860 ኪ.ግ የነበረውን የማር ምርት በ1999/2000 126700 ኪ.ግራም የማር ምርት ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡
- የተሻሻሉ የመኖ ልማትን ከማስፋፋት አንጻር የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን በአርሶ አደሩ አማካይነት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እንዲለማ የሚደረግ ሲሆን ይህም በ1997/98 ዓ.ም 1950 ሄ/ር ለምቶ የነበረውን በ1999/2000 ዓ.ም በ3092 ሄ/ር የተለያዩ የመኖ ዝርያዎች ማልማት የሚቻልበት የአሰራር ሥልት ይቀየሳሉ፡፡
- የቆዳና ሌጦ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለገበያ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት በ1997/98 ዓ.ም በቁጥር 1¸078¸908 ለማዕከላዊ ገበያ የቀረበ ሲሆን በቀጣዩ በ1999/2000 እስከ 1¸268¸686 ለማድረስ ታቅዷል፡፡
- የእንስሳት ጤና አገልግሎት፣ ለእንስሳት ምርትና ምርታማነት መሻሻል የእንስሳት የውስጥና የውጭ ጥገኛ በሽታዎች መከላከያ ክትባትና ሕክምና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ ከእንስሳት በሽታዎች ውስጥ አደገኛ በመሆን የሚፈረጀው የገንዲ በሽታ አምጪ የሆነው የቆላ ዝንብን ለመከላከል ስትራቴጂ ተቀይሶ በስፋት እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

## 3.5 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ

በዞርፉ ከሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት መሐከል የተፈጥሮ ደኖችን የመጠበቅና በአግባቡ ጥቅም ላይ የማዋል የተፈጥሮ ደን በተራቆተባቸውና የአፈር መሸርሸር በሚከሰትባቸው አካባቢዎች ተፋሰስን መሠረት በአደረገ ሁኔታ የአፈርና ውሃ ጥበቃ የደን ልማት ሥራዎች ሕብረተሰቡን በማሳተፍ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት፡-

- በአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ በ1997/98 1394 ኪ.ሜ የተለያዩ የእርከን ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን በ1998/99 2190 ኪ.ሜ. የእርከን ሥራ የሚከናወን ሲሆን በ1999/2000 ወደ 3285 ኪ.ሜ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡
- በደንና አግሮፎርስትሪ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የዛፍ ችግኞችን በማፍላት በ1997/98 በመደበኛ በአግሮፎርስትሪ 3¸119¸850 ችግኞች የተተከሉ ሲሆን በ1998/99 6¸844¸650 ችግኞች ለመትከል ታቅዷል፡፡ ይህንንም በ1999/2000 ወደ 10¸266¸975 ችግኞች ለመትከል ግብ ተጥሏል፡፡
- የተጐዱና የተራቆቱ መሬቶችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ በመከለል እንዲያገግሙ በማድረግ በ1997/98 ዓ.ም 321.2 ሄ/ር የተከለለ ሲሆን በ1998/99 1113 ሄ/ር በ1999/2000 2226 ሄ/ር በማሳደግ የሚከለል ይሆናል፡፡

## 3.6 የሕብረት ሥራ ማህበራትና ግብይትን በተመለከተ

በዞናችን የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በግልና በተናጠል ሆነው መቅረፍ የማይቻላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ችግሮችን በጋራና በተባበረ ሀይል መቋቋምና በሂደትም ወደ ተሻለ የእድገት ደረጃ እንዲደርስ በተለያየ አይነት የሕብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀትና በተደራጁ ማህበራት የሚካሄደውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ የማስፋትና የማጠናከር ሥራ አማራጭና ተተኪ የሌለው ተግባር ነው፡፡

በዚሁም መሠረት

- <u>አዳዲስ ማህበራትን ማደራጀት</u>

  የተለያዩ ለገበሬው ጠቀሜታ የሚያስገኙ እንደ ግብይት፣ ብድርና ቁጠባ፣ መስኖ፣ የእደ ጥበብ፣ ሸማቾች ...ወዘተ ማህበራት ትኩረት ተሰጥቶ በስፋት የሚደራጁ ሲሆን በዚሁም መሠረት እስከ 1999/2000 ዓ.ም ቀድሞ ከነበሩት በተጨማሪ 54 አዲስ የኅብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀት ተግባር ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በተደራጁ የአርሶ አደር የግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር 11 ቅርንጫፍ ማኅበር ለመክፈት ታቅዷል፡፡

- <u>የግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት</u>

  ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲንና የልማት ስትራቴጂን ስኬታማ ለማድረግና የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሣደግ የግብርና ግብዓት በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት

አርሶ አደሩ በአቅራቢያው እንዲያገኝ ማድረግ ቁልፍና ዋነኛ ተግባር ነው፡፡ ለዚህ ሥራ መሣካት አቅምን ያገናዘበ ዕቅድ ማቅረብ በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ጨረታ በወቅቱ ማውጣትና አቅርቦቱን የመከታተልና መረጃ የማደራጀት ሥራ በትኩረት ይሠራል፡፡

በዚህም መሠረት ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልግ ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር በተያዘው ዕቅድ መሰረት በኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

- **የሰብል ግብይትን በተመለከተ**

የዞናችን ግብርና ምርትና ምርታማነት በዘላቂነት እያደገ እንዲቀጥል ገበያን በማረጋጋት ወይም የምርት ዋጋ መዋዠቅን በመከላከል አርሶ አደሩ ላመረተው ምርት ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኝበት የገበያ ሁኔታ ለመፍጠር በኅ/ሥ/ማኅበራት የምርት ግብይት ሥራ በትኩረት የሚከናወን ሲሆን አብዛኛው የግብይት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሰብል ምርት ግብይት ሥራ በንቃት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

## 3.7. የክረምት የግብርና ሥራችን የእቅድ አፈጻጸም ስልት

በያዝነው የምርት ዘመን እንደርስበታለን ብለን ያቀድነው ከፍተኛ የሰብል ምርት መጠን ከወዲሁ በከፍተኛ ብቃትና ቁርጠኝነት ካላከናወነው የሚሳካ አይደለም፡፡ ስለሆነም አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችና አሰራሮች በመከተልና በመተግበር በጠናከረ የኤክስቴንሽን አሰጣጥ ታግዞ መሰራት ይኖርበታል፡፡

ዕቅዱን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የሚከናወኑ ተግባራት

- የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ በሪኮሜንዴሽኑ መሰረት መጠቀም
- የምርጥ ዘር እጥረትን ለመቀነስ አርሶ አደሩ በእጁ ያለውን የአካባቢም ሆነ ሌላ ዘር አበጥሮና አዘጋጅቶ በጥንቃቄ ማስቀመጥ
- የባለፉት ዓመታት ብድርና የዘመኑ ቅድመ ክፍያ በወቅቱ ገቢ ማድረግ
- በልማት ሰራተኞች አማካኝነት በየአካባቢው የሚሰጥ ወቅታዊ ስልጠና መከታተል
- የተለያዩ የውሃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም በበጋ ተጨማሪ ምርት ለማምረት ከወዲሁ መዘጋጀት
- ባለሙያውና የልማት ሠራተኛውን በተደራጀ ሁኔታ ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ለአርሶ አደሩ ወቅታዊ የሆነ የሙያና የቴክኒክ እገዛ በተከታታይ መስጠት
- በዞናችን ውስጥ ካለው ሊታረስ ከሚችለው መሬት 60 ከመቶ ብቻ የታረሰ በመሆኑ በዚህ ክረምት ተጨማሪ መሬቶችን ወደ ምርት ተግባር ማስገባት
- ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ሚና ያላቸው
    - መሬትን ደጋግሞ ማረስና ማለስለስ
    - በወቅቱ መዝራት
    - ደጋግሞ ማረምና መኮትኮት የመሳሰሉ ተግባራት በጥራት ማከናወን
- ለችግኝ ተከላ የጉድጓድ ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግና ተከላውን በአግባቡ በማካሄድ የችግኝ እንክብካቤ ስራዎችን ማጠናከር

- የቴክኖሎጂ ስርጸትን ለማስፋት አርሶ አደሩ በየልማት ቡድኑ በመደራጀት ከባለሞያ የሚቀርብለትን ምክርና ድጋፍ በትኩረት መከታተል
- የእርሻ መሬቶችን በውሃ ከመሸርሸር ለመታደግ የጠለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በግልና በጋራ ማከናወን
- የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ስርጭት በጊዜና በጥራት ማከናወን::

**4. ማጠቃለያ**

ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን ዕቅዶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ከአርሶ አደሩ ጀምሮ በየደረጃው ያለው አስፈጻሚ አካል ማለትም የአመራር አካላትና ባለሙያዎች ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብና በተቀመጠውም የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከማስፈጸምም ሆነ ክትትል በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ተገንዝበው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል::

## «ተባብረንና ጠንክረን በመስራት ድህነትን ታሪክ እናደርገው»